# ስለ አማራጭ ፕሮግራም አቀራረፅ (16/09/2004)

የምርጫው ተልእኮ መድበለ ፓርቲ ስርአት ምርጫ የሚቻልበት ሁኔታ ለማምጣት የምንችልበት ሁኔታ ለማመቻቸትና የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ወገናዊ የሆኑ ፕሮግራማቸውን ይዘው ህዝብ ፊት መቅረብ የሚችሉበት ዴሞክራሲያዊ የህገ መንግስት ስርአት ለማምጣት ነው። በዚህ ነጥብ ላይ አጠቃላይ ስምምነት ከተደረሰ ስለ ጋራው ፕሮግራም ይዘት፤ አላማ፤ የትኩረት ነጥቦች፤ አቀራረብና የማርቀቅ ሂደት ያለንን ሃሳብ እንደሚከተለው ባጭሩ እናቀርባለን።

1. የሽግግሩ ዘመን ፕሮግራም ጥንድ ይዘት

ሰነዱ የሽግግር መንግስት ፕሮግራም ብቻ መባሉ መጀመሪያውኑ በዚህ የምርጫ ሂደት የገባንበትን አላማ ሙሉ በሙሉ አያንፀባርቅም። ሁለተኛ ደግሞ የመንግስት አስተዳደር ፖሊሲን የሚመለከቱ ነጥቦች ላይ ብቻ ማተኮር ህብረተሰባችንን እንዳለ ከፀረ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለማሸጋገር የሚጠበቁንን የዴሞክራታይዜሽን ተግባራት ወደ ሁለተኛ ደረጃ አውርዶ ትኩረት ይነሳቸዋል። ስለሆነም በኛ ግምት ፕሮግራሙ የሽግግሩን ዘመን ጥንድ ተግባራት በሚያካትት መልክ የሚቀረፅና ጥንድ ይዘት የሚኖረው ሰነድ መሆን ይኖርበታል። በአንድ በኩል በሽግግሩ ዘመን በመንግስትነት የሚሰየመው ሃይል በተግባር የሚተረጉመው የሃገር አስተዳደር ፕሮግራም ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሽግግሩ እንዲሳካና እስኪሳካ ድረስ መተግበር የሚኖርባቸውን የህብረተሰቡ ዴሞክራታይዜሽን ተግባራትንና የጊዜ ቀመርን የያዘ ሰነድ መሆን ይኖርበታል። በዚህም የተነሳ ራሱ የሰነዱ መጠሪያ "የሽግግር መንግስት ፕሮግራም" ከሚባል "የሽግግር ዘመን ፕሮግራም" ቢባል አላማችንንና ተግባራችንን በተሻለ ይገልፃል የሚል እምነት አለን።

2. <u>የሽግግሩ ዘመን ፕሮግራም</u> አላማ

ፕሮግራሙ ሲረቀቅ " ብናሸንፍ በተግባር የምንተረጉመው" ከሚል አንድ ወጥ የሆነ ስሌት ብቻ ተነስተን የምናረቀው ሰነድ መሆን የለበትም። ከዚህ ይልቅ በሶስት የተለያዩ ፖለቲካዊ ክስተቶች አኳያ የጋራ ትግላችንን ለማፋፋምና ለመቀጠል እንደሚያስችል ሆኖ ቢሰናዳ የተሻለ ይሆናል። አንደኛ በሱ ዙሪያ ህዝባችንን ለማንቀሳቀስን በዚህም ለድል ከበቃን በተግባር የምንተረጉመው የድርጊት (የአክሽን) ፕሮግራም መልክ እንዲኖረው ያስፈልጋል። ሁለተኛ ህዝባችን በዚህ ፕሮግራም አምኖበትና በትግሉ ወቅት ተሰውቶለት ሳለ ኢህአዴግ በማጭበርበር አሸነፍኩ ካለ የፈቀደውን አማራጭ ለመምረጥ መብቱን የተነፈገውና ድሉን የተቀማው ህዝብ እንደ ጆርጂያ ወዲያውኑና በሽፍጡ ማግስት በቁጣ ተነስቶ ትግሉን የሚቀጥልበት ሰነድ መሆን ይኖርበታል። ሶስተኛ በኛ በኩል በተለያዩ የራሳችን ችግሮችና ድክመቶች ምክንያት አላማችንን ለህዝብ ማስጨበጥ አቅቶን ኢህአዴግ "በሃቅ" ሊያሸንፍ ይችላል የሚለውን ክስተት ከስሌታችን ጨርሶ ማውጣት አይቻልም። የኛ እምነት ኢህአዴግ በዚህ መልክ ካሸነፈ የሚከተላቸው አጥፊ ፖሊሲዎች የህዝባችንን ችግሮች እያባባሱ ይሄዳሉ። በመሆኑም የጋራ ፕሮግራማችን እስከ ቀጣዩ ምርጫ ብለን ለአምስት አመት የምናስተኛው ሰነድ ሳይሆን እየተባባሱ ለሚሄዱት ለእለት ከእለት የህዝባችን ችግሮች መፍትሄዎች እየጠቆመ ትግሉን ለመቀጠል በሚያስችል ሁኔታ መሰናዳት ይኖርበታል። በቀጣዮቹ አመታት ሰላማዊ ሰልፍም ሆነ የስራ ማቆም አድማ ከዚያም አልፎ የሲቪል "ዲስኦቢዲያንስ" እንቅስቃሴ ለማካሄድ የምንጠቀምበት የትግል መሳሪያ ሆኖ መቅረብ ይኖርበታል።

3. የሽግግሩ ዘመን ፕሮግራም አቀረብ

ከፍ ብለን እንዳልነው ይህ ፕሮግራማችን በተለያዩ የፖለቲካ ኮንቴክስቶች ህዝብ የምንቀሰቅስበትና ታግለን የምናታግልበት ሰነድ በመሆኑ አማራጭነቱ የት ላይ እንደሆነ እጅግ ጎልቶ መታየት ይኖርበታል። እንደ "ተራ" የፖለቲካ ፓርቲ ፕሮግራም በትምህርት በኩል ይህንን ያደርጋል፤ በእርሻ ይህንን ፖሊሲ ይከተላል፤ የሴቶች እኩልነት ይረጋገጣል ወዘተ በሚል መልክ የራስን አቋም ብቻ በመዘርዘር መወሰን የለበትም። ከዚህ ይልቅ በየመስኩ በጋራ የምንታገለውን የኢህአዴግን አጥፊ ፖሊሲ በሚያጋልጥና እዛው በዛው ደግሞ ከዚህ ጥፋት በማድረስ ላይ ካለ ፖሊሲ አንፃር ለህዝባችን የምናቀርበውን ተጨባጭ አማራጭ በሚያቀርብ መልክ መዘጋጀት ይኖርበታል።

4. የሽግግሩን ዘመን ፕሮግራም የማርቀቅ ዘዴ

ፕሮግራማችን በዚህ አማራጭነቱ ጎልቶ በሚታይበትና ተጨባጭ በሆነ መልክ እንዲሰናዳ ከፈለግን ጥቂት ሰዎች ቤት ዘግተውና ከተለያዩ የህብረቱ አባል ድርጅቶች ፕሮግራሞች "አውጣጥተው" ያርቅቁት ማለት አይቻልም። ከዚህ ይልቅ በድርጅት ከተካተቱም ሆነ ከዛ ውጭ ካሉ አገር ወዳድና ዴሞክራት ከሆኑ በየመስካቸውና በየሙያቸው የኢህአዴግን ፖሊሲዎች አጥፊነትና ሊቀርቡ ስለሚችሉ አማራጮች ምንነት ግንዛቤ ካላቸው ዜጎችና ማህበራት ጋር ግንኙነት ፈጥሮ አስተዋፅኦ የሚያደርጉበትን ዘዴ መሻት ያስፈልጋል። ከነዚህ ዜጎች ወይም ስብስቦች በአንድ በኩል በየመስካቸው በአንድ ገፅ የኢህአዴግን ፖሊሲ በሌላ ገፅ ደግሞ ፕሮፖዝ የሚያደርጉትን አማራጭ መጠየቅ ከዚያም በተጨማሪ የመጀመሪያውን ረቂቅ ለዘጋጀት ተመደብነው ግንዛቤ እንዲረዳን ሰነዳቸውን ለማዘጋጀት የተጠቀሙባቸውን ዋና ዋና ዶኩሜንቶች እንዲያስተላልፉ መጠየቅ ያስፈልጋል። በዚህ መልክ ከየአቅጣጫው የሚቀርቡት ሰነዶች ከተጠራቀሙ የሚቀረው ተግባር ለፕሮግራሙ መግቢያ መፃፍና ቀስቃሽ ገፅታቸውን እያጎሉ ማቀነባበር ይሆናል። ይህ በአጭር ጊዜ ተሰርቶ ለውይይት ለአባል ድርጅቶች ይቀርብና ከዚያ ለህዝብ ይፋ ይሆናል።

ማስታወሻ ረቡእ 16/09/04 ስለተነሱት ነጥቦች

4ኛ. ትግሉን ከመዝረክረክና አመኔታ ከማጣት ለማዳን፤ አገር አቀፍ ጉባኤና ተተኪ ካቢኔት

ከፍ ብለን እንደጠቆምነው የህዝባችን ተጋድሎ እዚህ ታሪካዊ ደረጃ የደረሰው ወዴት እንደምንሄድና ወዴትስ እንደምንወስደው ግልፅ አቅጣጫ ስላሳየነው ነበር። ዛሬ "ትግሉ ይቀጥላል" ከሚል ሌላ ተጨባጭ አቅጣጫ አለመያዝ የትግሉን መበተን ሊያስከትል የሚችልበት አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ነን። ይህ የአቅጣጫ መያዝ ነገር ለሃገራችንና ለህዝባችን ተጋድሎ ዛሬ የሞት ሽረት ጥያቄ መስሎ ስለሚታየን ከእንግዲህ መወሰድ ያለባቸው ሁለት እርምጃዎች በግልፅና በማያሻማ ሁኔታ መቅረብ ይኖርባቸዋል።

አንደኛ አገር አቀፍ የተወዳዳሪዎች ጉባኤ ጉዳይ ነው። እስካሁን የህዝባችንን ትግል አቅጣጫ እየሰጡ ሲመሩ የነበሩት ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በተለይ ህብረቱና ቅንጅቱ ከመላ ሃገሪቱ ተወዳዳሪዎቻቸውን ጠርተው በጣም በአስቸኳይ አንድ አገር አቀፍ ጉባኤ አዲስ አበባ መጥራት አለባቸው። ሁለተኛ ይህ ጉባኤ ከሚያከናውናቸው ታሪካዊና በርካታ ተግባራት አንዱ ተተኪ ወይም "ሻዶ" ካቢኔት ማቋቋም ይሆናል።

1. አገር አቀፍ ጉባኤ ስለመጥራት

*ይህ ጉባኤ ለምን ያስፈልጋል? ተግባራቱስ ምንድን ናቸው?*

ትግሉ አገር አቀፍ ቅንብር ማግኘት የሚኖርበት መጀመሪያው ም-ክንያት ከወዲሁ ለተጀመረውና ትግሉ ከተበተነ መጠን ስቶ ሊቀጥል ለሚችለው ቀጣይ የአፈና ውርጅብኝ በሩን ለመዝጋት ነው። ዛሬ ህብረተሰቡ ከዳር እስከዳር ተንቀሳቅሶና በሃገሪቱ በርካታ አለም አቀፍ ታዛቢዎች ባሉበት ሁኔታ እንኳን በመካሄድ ላይ ያለውን የአፈና፤ የእስራትና የግድያ ዘመቻ በአይናችን ስር እያየነው ነው። ነገ እኛም "ዲሞቢላይዝድ" ስንሆን ፈረንጆቹም አገር ለቀው ሲወጡ ይህ አፈናና ወከባ መረን በለቀቀ ሁኔታ የሚስፋፋበት አደጋ አለ። ቀደም ሲል "ምርጫው ይለቅና እንተያያለን" የሚል የካድሬዎች ዛቻ እንደነበር እናውቃለን። ዛሬ ከአሁኑ በዚህ ውርጅብኝ ተሰማርተዋል። ጎንደር አፍንጫ ሲመታ ኢሉባቡር አይን እንደሚያለቅስ፤ አገር አቀፍ ቅንብር ማጣታችንን ተማምኖ ወያኔ ኢህአዴግ ሁላችንንም ተራ በተራና ብቻ ለብቻ በፈለገው ሰአት፤ የፈለገውን አካባቢ፤ በፈለገው ህገ ወጥ የአፈና ዘዴ እያጠቃሁ ህዝቡን ተስፋ መቁረጥ ባህር ውስጥ እጨምረዋለሁ ብሎ ቢያልም ይህንን ሴራና አፈና ለመቋቋም ህብረተሰባችን እንኳን ሊበተን ቀርቶ ትጥቅ እንዳልፈታና ከትላንቱ ይልቅ በይበልጥ ተደራጅቶ በአገር አቀፋዊ ቅንብሩ ደምቆ በተጠንቀቅና በትግል ላይ ያለ ህብረተሰብ መሆኑን ማሳየቱ ህዝቡም ትግሉን በሞራል እንዲቀጥል፤ ኢህአዴግም የዚህን ህዝብ ትግል እንደዋዛ እንዳይወስደው የሚረዳ ታሪካዊ እርምጃ ነው።

ሁለተኛ ይህ የምርጫ ማግስት ጉባኤ አስፈላጊ የሚሆነው የምርጫውን ውጤት በጋራ በመገምገም እንደሁኔታው በመንግስትነትም ሆነ በተቃዋሚነት ስለምናካሂደው ትግል አቅጣጫ መቀየስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው። በሃቅ ከተቆጠረ እናሸንፋለን መንግስት ይዘን አገር እናስተዳድራለን ካልን ውጤት ሲታወቅ ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ የምንል ከሆን ለአላስፈላጊና (በኢህአዴግም ሊታገዝ ለሚችል) አለመጋጋት በር በመክፈት የህዝባችንን ድል መልሰን የምንነጠቅበት አደገኛ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። በመሆኑም በዚህ ጉባኤ ላይ ከህብረቱም ከቅንጅቱም ከሌሎቹም ፕሮግራሞች የተውጣጣ አንድ የጋራ ፕሮግራም መንደፍ አንገብጋቢ ይሆናል። በሌላ በኩል ደግሞ ምንም እንኳዋን የማይመስል ቢሆንም ኢህአዴግ በአሸናፊነት ከወጣ ይህንን በፀጋ ብንቀበልም በቀጣዮቹ አመታት ትግል አይኖርም ማለት አይደለም። ኢህአዴግ "በሃቅ" ቢያሸንፍ እንኳን ይህንን ጊዜያዊ ሽንፈት በፀጋ መቀበል ማለት እስከ ቀጣዩ ምርጫ የኢህአዴግን አጥፊ ፖሊሲዎች አሜን ብለን እንቀበላለን ማለት አይደለም። ይህ ድርጅት የሚከተለው ፖሊሲ ፀረ ህዝብ ፖሊሲ በመሆኑ የሃገራችን ችግሮች ማለትም ድህነት፤ ርሃብ፤ ስራ አጥነት፤ የአካባቢ ውድመት፤ በሽታ....እየተባባሱ እንጂ እየተቀረፉ አይሄዱም። በየትም ዴሞክራሲያዊ አገር ብንሄድ ተቃዋሚዎች የምርጫ ውጤት ቢቀበሉም በምርጫ የመጣ መንግስትን ፖሊሲ ተቃውሞ መታገል በየትም ያለ የዴሞክራሲ አሰራር ስለሆነ እኛም ተጨባጭ አማራጮቻችንን አንግበን በነዚህ ዙሪያ ህዝባችንን እያንቀሳቀስን ትግሉን እንቀጥላለን ማለት ነው። በአገር

ደረጃ እየተስፋፋ በመሄድ ላይ ያለ ክስተት ሆኗል። በያለበት በዩክሬን ሆነ በጆርጂያ፤ በኪርጊክስታን ሆነ በቶጎ ዴሞክራቶች የገዥዎችን ሸፍጥ ተቃውመው በድል አድራጊነት መውጣት የቻሉት ስለሸፍጡ ግልፅና አሳማኝ መረጃዎች በማቅረብ ህዝባቸውንም ሆነ አለም አቀፍ ኮሙኒቲውን ከጎናቸው በማሰለፋው ነው። እንደኛ ሰፊና በትራንስፖርትና ኮሙኒኬሽን ብዙ እርምጃ ባላደረገች አገር እነዚህን በየምርጫ ጣቢያው የተደረጉ ሸፍጦችን በአሳማኝ ሁኔታ መረጃ ለመሰብሰብ ከሁሉ የሚቀለውና የሚፈጥነው ዘዴ ራሳው እጩዎቻችን መረጃቸውን ሰብስበው አዲስ አበባ መሰብሰባው ነው። በዚህም የተነሳ ስለምርጫው ሂደት እያንዳንዱ እጩ የሆነውን ሁሉ በሃቅ መዝግቦና በተጨባጭ ማስረጃዎች አስደግፎ በተወዳደረበት አካባቢ የሆነውን ሁኔታ ይዞ መምጣት ይኖርበታል። በዚህ ጉዳይ ከወዲሁ ለኢህአዴግም፤ ለኢትዮጵያ ህዝብም ለአለም አቀፉ ኮሙኒቲም ሁለት ነገሮች በጣም ግልፅ ማድረግ ይኖርብናል። ከነዚህ መረጃዎች ተነስተን ሶስት አይነት እርምጃዎች ልንወስድ እንችላለን

አንደኛ በያለበት የተወሰኑ ማጭበርበሮች የተከሰቱ ቢሆንም ኢህአዴግ ማጆሪቲ ያመጣው ሳያጭበረብር ከሆነ እኛ ራሳችን ለህዝባችን አማራጭ ስናቀርብ በተለያዩ የውስጥ ድክመቶችና የስትራቴጂና ታክቲክ ስህተቶች በቂ ተአማኒነት እንዳላገኘን መሆኑን በይፋ አምነን መቀበል ይኖርብናል። የደረሰውን ሽንፈት በፀጋ ተቀብለን መግለጫ እናወጣለን። ይህ አይነቱ አካሄድ በኛ ግምት በሃገራችን ዴሞክራሲ መዳበር አይነተኛ አስተዋፅኦ ከማበርከቱ በላይ ይበልጥ ወደ ራሳችን አተኩረን በሃቅ ከስህተቶቻችን ለቀጣዩ ትግል ትምህርት ለመቅሰም ይረዳናል ብለን እናምናለን። ይ-ህ ስለተባለ ግን አጠቃላይ ውጤቱንና የደረሰውን ሽንፈት ብንቀበልም በተወሰኑ የምርጫ ወረዳዎች እጩዎቻችን የተሸነፉት በመረጃ በተደገፉ ህገ ወጥ ድርጊቶች መሆኑ ከተረጋገጠ በጋራ ሆነን ምርጫዎች በነዚህ አካባቢዎች እንዲደገሙ መንቀሳቀስ ይኖርብናል።

ሁለተኛ በየአካባቢው የተደረጉት ማጭበርበሮችና የተከሰቱት ህገ ወጥና ፀረ ነፃ ምርጫ ድርጊቶች ተዘርዝረው ከተመዘገቡ በሁዋላ በሚደረገው ስሌት ኢህአዴግ ማጆሪቲ ያገኘው በሸፍጥ መሆኑ ከተረጋገጠ ይ-ህንን በማስረጃ በተደገፈ ሪፖርት/መግለጫ ለኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ ለአለም አቀፉ ኮሙኒቲ አስታውቀን የምርጫውን ውጤት እንደማንቀበል ይፋ እናደርጋለን። ይህ ምርጫ ተሰርዞ ሌላ እንዲዘጋጅ ከአዲስ አበባ ጀምሮ በሌሎችም አካባቢዎች የስራ ማቆም፤ የሰላማዊ ሰልፍና የሌሎች የሲቪል ዲስኦቢዲያንስ ትግሉን ሳናሰልስ በአንድነት እንቀጥላለን ማለት ነው።

ሶስተኛ ይህንን ግልፅ ስትራቴጂ ካሁኑ ይፋ ማድረግና " በሃቅ ከሆነ እንቀበላለን በተጭበረበረ ሁኔታ ከሆነ ግን ህጋዊ፤ ሰላማዊና ህዝባዊ ትግላችንን በተዘበራረቀ ሁኔታ ሳይሆን በጥሞናና በተደራጀ መልክ የሚካሄድ ትግል ለመቀስቀስ እንሰራለን" ብሎ ይፋ መግለጫ ካሁኑ መውጣት አለበት። እንዲህ አይነቱ አካሄድ ቢያንስ ሶስት ጥቅሞች አሉት። አንደኛ የኡህአዴግን "የምርጫ ማግስት የአመፅ ሴራ" የሚል ፕሮፓጋንዳ እናከሽፋለን። ሁለተኛ ትግሉ በተደራጀና አገር አቀፍ ቅንብርና አመራር ባለው ሰላማዊ ስልት እንደሚካሄድ ካስታወቅን የህዝባችንን የትግል ሞራል ከማንሳቱ በላይ ኢህአዴግ በአለም አቀፍ ደረጃ "ለሽብር ፈጣሪዎች የሚመች አለመረጋጋት ሊፈጥሩ ነው" ብሎ የተሰማራበትን ፕሮፓጋንዳ ልናከሽፍ እንችላለን። ሶስተኛ የኢህአዴግ መሪዎች ይህ ቁርጠኛነት እንዳለና ይህ በየመንደሩ የተፈፀመ ህገ ወጥ ድርጊት ተመዝግቦ በመአከል ደረጃ አዲስ አበባ ይፋ እንደሚሆን ማስጠንቀቂያ ከደረሳቸው ከህገ ወጥ ድርጊቶች የመቆጠባቸው እድል እንደሚጨምር መረዳት ከባድ አይመስለንም።

## 4. ለቀጣዩ አገር አቀፍ ትግል ሁኔታዎችን ለማመቻቸት

በኛ ግምት በተለይም አሁን የቅንጅቱን "የም-ርጫ ማኒፌስ-ቶ" ከተመለከትን በሁዋላ በሁለቱ ስብስቦች መሃከል ጎልቶ የሚታይ ልዩነት አለ። የኛ እስከዚህም ድረስ የምርጫ ሳይሆን የትግል ማኒፌስቶ ነው። ይህ ሰነዳችን በዚህ ምርጫ ካልቀናን ጊዜ ጠብቀን በቀጣዩ ግንቦት መልሰን የምናቀርበው የምርጫ ሰሞን ሰነድ አይደለም። ግንቦት መጣ ሄደ የኢህአዴግ የተሳሳቱ ፖሊሲዎች አሉ። ይኖራሉ። ግንቦት መጣ ሄደ ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ያቀረብናቸው አማራጮች ቀጣዩን ምርጫ ጠብቀን የምንንቀሳቀስባቸው አይደሉም። ኢህአዴግ "በሃቅ" ቢያሸንፍ

እንኳን ስራ አጥነትን፤ ድህነትን፤ የአካዳሚ ውድመትን፤ ርሃብን፤ የብሄራዊ ኢኮኖሚ ግንባታን አስመልክተን ባቀረብናቸው አማራጮች ዙሪያ ሳናሰልስ እንደምንታገል ከወዲሁ "ለሚመለከተው ሁሉ" ግል-ፅ ማድረግ ይኖርብናል። የምርጫውን ውጤት እንቀበላለን ስንል አንድ ነገር ግልፅ መሆን አለበት። የኢህአዴግ መንግስት ፖሊሲዎች የሃገራችንን ችግሮች እያባባሱ ህዝባችንንም ከቀን ቀን መቆሚያ መቀመጫ እያሳጡ እንደሚሄዱ ጥርጥር ሊኖር አይችልም። በመሆኑም አጥፊ ፖሊሲ ፋታ የነሳው ህዝብ ለዚህ አገዛዝ ፋታ ሳይሰጥ ትግሉን መቀጠል ይኖርበታል። ይህ ደግሞ የዴሞክራሲ አንድ ዋና ገፅታ ነው። በመሆኑም ይህ ጉባኤ ያለፈውን ከመገምገምና ተገቢ ውሳኔዎችን ከመውሰድ አልፎ ስለቀጣዩ ትግል ስትራቴጂ የሚቀየስበትና ለዚህ ትግል ደግሞ አስፈላጊው ድርጅታዊ አወቃቀር መሰረት የሚጣ)በት ጉባኤ ይሆናል ማለት ነው። በዚህም መሰረትሁለት ተግባራት ይኖሩታል

አንደኛ የጋራ ትግሉን ፕሮግራም ማዳበር - በዚህ ጉባኤ ላይ ከየአካባቢው የመጡትና በየአካባቢያቸው በህብረተሰቡ ው-ስጥ የተተከሉ እጩዎቻችን በካምፔይኑም ወቅት ህዝቡ ካንፀባረቀቻው ችግሮችና ብሶት እንዲሁም ለነዚህ ከህዝብ ከተሰነዘሩ የመፍትሄ ሃሳቦችም ሆነ በአጠቃላይ ካላቸው ተመክሮ ተነስተው ከሰነዱ አንፃር ተረሳ፤ ይበልጥ ተጨባጭ ይሁን፤ ይ-ስተካከል እያሉ ከሚሰነዝሩዋቸው ሃሳቦች በመነሳት ከአሁኑ የዳበረ ይበልጥም ተጨባጭነት ያለው የተዋጣለት የአገር አቀፍ ትግል መሳሪያ ሰነድ መዘጋጀት ይኖርበታል። ለዚህም ሲባል አስፈላጊ ከሆነ በየመስኩ ኤክስፐርቶችን መጋበዝና ግንዛቤ እንዲያስጨብጡ ማድረግ ይችላል።

ሁለተኛ በአገር አቀፍ ደረጃ የተዋቀረ በየክልሉ ተጠሪ አካላት ያሉት አስተባባሪ ኮሚቴ ማቋቋም ለቀጣዩ ት-ግል በዚህ መልክ መዋቅራዊ ህልውና ካልሰጠነው ያው ካለፈው ጊዜ ከተደረገው ስህተት ሩቅ አይደለንም ማለት ነው። በመኢሶን በኩል ከሁለት አመት በፊት ይህ አካል "ተተኪ ሸንጎ" እንዲባል ሃሳብ ቀርቧል። ይህ አጠራር ኢህአዴግ እንደሚለው ምንም የአመፅ ገፅታ የለውም። ከዚህ ቀደም አማራጭ ምክር ቤት ብለን ማቋቋማችን ምንም አመፅ አልነበረም። ምንም በህገ መንግስቱ የተከለከለ ነገር አይደለም። አወቃቀሩን በተመለከተ በኛ በኩል የሚቀርበው ሃሳብ የመንግስት ፖሊሲዎችን "የም-ንለውን እያወቅን" ለመቃወምና የምናቀርበው አማራጭ በተጨባጭነቱ እየጎላ እ-ንዲሄድ ከሁሉም በላይ ደግሞ ተአማኒነት እንዲኖረን የሚፈጠረው አካል ቢያን-ስ በመአከል ደረጃ "የሻዶ ካቢኔት" መልክ መያዝ ይኖርበታል እንላለን። ለየመስኩ የሚመደቡትን ሰዎች ሚኒስትር ባንላቸውም የእርሻ፤ የአካባቢ ጉዳይ የጤና፤ የኤችአይቪ ኤይድስ፤ የወጣቶች፤ የሴቶች ወዘተ ጉዳይ ሃላፊ እያልን ብቃት ያላቸው ዜጎች መሰየም ይኖርብናል። አለበለዚያ እንደ እስካሁኑ ሁሉም በሁሉም "ኤክስፐርት" የሚሆንበት አሰራር ከተከተልን "ተቃዋሚዎች ምንም አማራጭ አያቀርቡም" የሚለውን የኢህአዴግ ፕሮፓጋንዳ ማገዝ ይሆናል።

## ሌሎች ነጥቦች

1. በውጭ የሚካሄደው ትግል ቀጣይነት ጉዳይ - በዚህ መስክ እስካሁን ብዙ የሚያኮራ ት-ግል ተካሂዷል። አሁንም እንደ COFFEE እና EAC አይነቶቹ ስብስቦች ብዙ እየታገሉና ውጤት እያስመዘገቡ ናቸው። ሆኖም ይህ ትግል በኛ ግም-ት በነፃ ምርጫ ጉዳይ እ-ስካተኮረ ድረስና በተለይ ለውጭው አለም ኢህአዴግ ደረቱን ሰጥቶ በተቀመጠበት በህገ መንግስቱ ጥያቄም ላይ ካላተኮረ በዚህ ሃይል ላይ የማያወላዳ የበላይነት የማግኘታችን እ-ድል እስከዚህም አይደለም። እኔም በነፃ ምርጫ አምናለሁ፤ ለዚህ የተሻለውን ሁሉ እየሰራሁ ነው፤ ከፈለጋችሁ ኑር ታዘቡ፤ ሌላው ቀርቶ በጉዳዩ ከተቃዋሚዎች ጋር ተቀምጬ እየተደራደርኩ ብቻ ሳይሆን እንዲያውም ካቀረቡት 29 ጥያቄ 27ቱን አስተናግጃለሁ....እያለ የሚንቀሳቀስ ሃይል ነው። ይህ ደግሞ ይሰራለታል። በቅርቡ በአሜሪካ አንዳን-ድ የኮንግረስ ሰዎች ይህንኑ መከራከሪያ በማቅረብ በም-ክር ቤቱ እንዲያልፍ የሚሞከረውን ቢል ላለመደገፍ መወሰናቸው በዚህ በኩል የኢህአዴግን ሎቢ ለመቋቋም ች-ግር እንዳለ አሳይቶናል። ባጭሩ ነፃ ምርጫ የሚለው እንቅስቃሴ ከዴሞክራሲያዊ ህገ መን-ግስት ከሚለው ጋር ካልተያያዘ ተአማኒነቱ ውሱን ነው። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ በዚህ አላማ ብቻ ከተወሰነ በወር በወር ተኩል ውስጥ በዲፕሎማሲው መስክ ያው የተለመደውን አፈናና መብት ረገጣ ከማጋለጥ ያለፈ ትግል ለማካሄድ የማን-ችልበት ሁኔታ ይፈጠራል። ስለዚህ በኛ ግም-ት በዚህ ትግል መስክ የተሰማሩ

ወገኖቻችንና የድጋፍ ኮሚቴዎች አላማውን ሰፋ አድርገው የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ በጣም ባስቸኳይ (ማለትም ከምርጫው በፊት) መመቻቸት ይኖርበታል ማለት ነው።

2. በምርጫው ማግለስት ትግል ቅንጅቱንም የማሳተፉ ጉዳይ - ህብረታችን ከፍ ብለን በጠቀስነው መሰረት ስለቀጣዩ ትግል ያለውን ስትራቴጂ ከተቀበለ በጉዳዩ አንድ መግለጫ ባስቸኳይ መውጣት ይኖርበታል። በሚቀርበው ስትራቴጂ ተስማምቶ በዚህ ሂደት ከኛ ጋር እንዲተባበር ለቅንጅቱ ይፋ የሆነ ጥሪ ቢደረግ መልካም ይመስለናል። የሆነ ሆኖ በዚህ ሂደት እምቢም ላለማለት እሽም ላለማለት ተቸግረው አላስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን የሚደረድሩ ከሆነ ያለውን የአካሄድ ልዩነት ለደጋፊዎቻችንም ሆነ ለኢትዮጵያ ህዝብ ይፋ አድርገን የራሳችንን የቀጣይ አገር አቀፍ ትግል ስትራቴጂ በተግባር ለማዋል መንቀሳቀስ ይኖርብናል።